PANORAMA # 9

<u>የትዝብት አድማስ</u>

ጥር 9 2000 ዓም

<u>ለዳግም ምዕዓቱ</u>

አንድ ሰውም ይሁን ሕዝብ በህይወቱ ሊታለል÷ ሊጎዳና ሊጠቃ የሚችለው አንድ ጊዜ ብቻ ሊሆን ይችል ይሆናል:: በተመሳሳይ ሁኔታና ጊዜ በተመሳሳይ አታላዮች ሊጭበረበር እራሱን ካዘጋጀ ግን÷ የአዕምሮውን ጤና መሆን እንደገና ሊመረምረው ይገባል:: "አንድ ሰው በመጀመሪያ ሲታለል÷ አታላዩን ውቀስው÷በድጋሜ የተታለለ እንድሆን ግን÷ የታለለውን ሰው እዘንበት እንጅ አትዘንለት" እንዲሉ÷ በተደጋጋሚ የአጭበርባሪዎች ሰለባ ለመሆን መዘጋጀት÷ ተጠቂው ክፍል አዛኝ እንዳያገኝ ማድርግ ይሆናል:: አታላዮች ደግሞ የሚያታልሉትን ወገን ማንነት በሚገባ አውቀነዋል ብለው ካመኑ÷ የተለያዩ የማታለያ ዘዴዎችን በመጠቀም ማጭበርበራቸውን ይቀጥሉበታል:: ይህ ሂደት ግን ለዘለዓለም የሚቀጥል አይሆንም:: ሕዝብ ይዘግይም ይፍጠን÷ አታላዩን በትዕግስት እየተከታተለው ከቆየ በኋላ ትዝብቱ ሲገነፍል÷ ማመጹ አይቀርም::

በሕዝብ ያልተመረጠ መንግሥት ያው አምባገነን መሆኑ ስለማይቀር÷ ጨቁኖ የሚገዛውን ሕዝብ ሊያምነውም ይሁን ሊያፈቅረው አይጠበቅበትም:: ይልቁንም የሚጠቀምበት የማታለያ ዘዴ በሕዝብ ዘንድ ታውቆብኛል ብሎ ካመነ÷ በአዲስ የመታልያ ዘዴ ለመጠቀም ለዚህ ዘዴው ተስማሚ የሆነ የፕሮፓጋንዳ ዘመቻውን ይጀምራል:: የወያኔ መሪዎች የኢትዮጵያን ሕዝብ ያታለሉ መስሎአቸው ወደ አዲስ አበባ ሲሄዱ በየአካባቢ ነዋሪዎች ዘንድ ተቀባይነት ያተርፍልናል ብለው በመገመት÷ ወሎ ሲገቡ÷ " ዘመቻ ዋለልኝ" ወደ ጎንደር ሲጠጉ ደግሞ÷" ዘመቻ ቴዎድሮስ" በሚል የፖለቲካ ዘማዊነትን እየተጠቀሙ ለዓላማቸው መምቻ አውለውታል:: ተወደደም ተጠላ ይህ ፕሮፓጋንዳ በጊዜው ጠቅሟቸዋል:: ይህ የሆነውም የኢትዮጵያ ሕዝብ ለወያኔ ካለው ፍቅር ሳይሆን÷ ለደርግ ከነበረው የከረረ ጥላቻ ምክንያት ነው:: ይህንን አጋጣሚ በሚገባ በመጠቀም ወያኔዎቹ የተነሱበትን ዓላማ በተግባር ለማዋል ብዙም አልተቸገሩበትም:: ኢትዮጵያን እንደ ሀገር ሕዝቧንም እንደ ዜጎች የማጥፋት ተልዕኳቸውን ለመፈፀም የቻሉ ለመሆናቸው ሀገሪቱ አሁን ያለችበት ሁኔታ በግልፅ ያሳያል::

የኢትዮጵያን ዕውነተኛ ታሪክ ወደ ሀሰት በመለወጥ÷ የሀገሪቱን ባዕዳን ጠላቶች በማሳመንም የጥፋቷ ተባባሪ እንዲሆኑ አድርገዋቸዋል::. እነኝህም የውጭ ጠላቶች ለነወያኔ ገደብ-የለሽ ትብብር እያደረጉላቸው ለመሆኑ ማንም የማይከራከርበት ሀቅ ነው:: ይህ እንዳለ ሆኖ÷ የወያኔ መሪዎች÷ ማንነት በሀገሪቱ ዜጎች ዘንድ በሚገባ ስለታወቀ÷ እንደ አሰቡትና እንደ ፕሮፓጋንዳ ጥረታቸው

ሀገሪቱን የመግዛት ኃይላቸው እየከሰመ፥ እህል-ውሀቸው እየተሟጠጠ በመሄድ ላይ ነው:: እነርሱም እራሳቸው፥ እያንገፈገፋቸውም ቢሆን፥ይህንን ክስተት በሚገባ ተረድተውታል:: መረዳታቸውን ለመገንዘብ፥ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የሚጠቀሙበትን የሀሰት ፕሮፓጋንዳ ዘዴ በቅጡ መገንዘብ ያስፈልጋል::

"ሌቦች የሚጣሉት ሲሰርቁ ሳይሆን፥ የሰረቁትን ሲከፋፈሉ ነው" እንደሚባለው ወያኔዎቹ ሥልጣን ከያዙ በኋላ፥ እርስ በእርሳቸው በስኳርና በሌላ ቆሳቁስ ሲራኮቱ፥ በመጀመሪያ ታምራት ላይኔ ቀጥሎም ስየ አብርሃ ወደ ወህኔ መወርወራቸው የታወቀ ነው:: ወያኔዎቹ እራሳቸው ብቻ በሚያውቁት ምክንያት፥ ታምራት በወህኒ ቆይቶ ስየ እንዲፈታ ሆኖ፥ ዛሬ፥ የወያኔን ሥርዓት ለመቀጠል በሚደረገው ሂደት ግንባር ቀደም ሚና እንዲጫወት እየተደረገ ይገኛል:: ስየ! ይህንን ሂደት የቀጠለውም፥ የበግ ለምድ በለበሰ የተኩላ ገፀ-ባኅርይ ለመሆኑ፥ ለማንም ኢትዮጵያዊ የተሰወረ አይደለም:: የስየ በአዲስ መልክ አዳዲስ የማታለል ሚና የመጫወት ዓላማ አንድ ብቻ ነው:: የወያኔን ሥርዓት በጥገናዊ ለውጥ ወሻሽሎ እንዲቀጥል ማድረግ ነው:: ስየ ይህንን ሙከራ በሚያደርግበት ወቅት ግንባር ቀደም ሚና እንዲጫወት የሚያስችለው መፈክር ብሔራዊ ዕርቅ ለማምጣት የሚል ሆኖ፥ በውስጥ ግን የወያኔን ፕሮግራም ለማስቀጠል የሚያስችለውን ሂደት ለማካሄድ ለመሆኑ ለማንም አስተዋይ ኢትዮጵያዊ የሚሰወር አይደለም::

ይህንን የማታለያ ተግባሩን በሚያካሂደበት ወቅት ማነኛቸውንም የወያኔን መንግሥታዊ ፖሊሲዎችንና አፈጻጸማቸውን እየተቸ አይደለም:: በአንፃሩ ግን ፥ በብሄረሰብ ላይ የተመሠረተውን የሀገሪቱን አከፋፈል ይደግፋል:: እርሱ በመሠረተው የህወሓት የፖለቲካ ፕሮግራም ላይ ተመርኩዞ የተፃፈውን የወያኔን ሕገ መንግሥት ሙሉ በሙሉ ይቀበላል:: ዜጎች ከፈለጉ ሊገነጣጠሉ ይችላሉ የሚለውን አንቀጽ 39ንም እንዳለ ያጸድቀዋል:: <u>የስየ ተቀዳሚ አጀንዳ፥ የሥልጣን ተፎካካሪውን፥ የጥቅም ባላንጣውንና ወደ ወህኒም የወረወረውን መለስንና ተባባሪዎቹን ከሥልጣን አስወግዶ፥ ለይስሙላም ቢሆን ውሽልሽል ጥገናዊ ለውጥ በማድረግ፥ መለስ አልባ ወያኔን ለማስቀጠል</u> ነው:: ስለ ኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነትና ብሔራዊ ጥቅም ደንታ የለውም:: የሀገሪቱንም ህልውና የስየና የግብረ አበሮቹ አጀንዳ አይደለም:: ይሆናል ተብሎም አይጠበቅም::.

ስየ አብረሃ፥ መለስን ለማውረድ ዝግጅቱም ሆነ ችሎታው ስለሌለው፥ ይህን ዓላማውን ለማሳካት የተቃዋሚ ድርጅቶችንና የኅብረተሰቡንም ትብብር ለመሻት ይጥራል:: አሁንም በአሜሪካ ሀገር በየቦታው እየዞረ የሚያደርገው የማታለያ ጥረትም ለዚህ ዓላማ ሲባል ብቻ ነው:: "አዛኝ ቅቤ አንጓች" እንዲሉ በብሄራዊ ዕርቅ መፈከር፥ የግል አጀንዳቸውን ለማራመድ በግድ የቀሪውን ኅብረተሰብ ድጋፍ ለማትረፍ ላይና ታች በመሯሯጥ ላይ ይገኛሉ:: " በጨው ደንደስ በርበሬ ተወደስ" እንዲሉ፥ በሌላው ትክሻ የራሳቸውን ጠባብ አጀንዳ ለማራመድ፥ በግድ የማታለል ጥረት ማድረግ አለባቸው::

በዚህ የእነርሱ የዳግም ምፅዓት ዙር የማታለል ሂደታቸውም፥ ውሃ ያልነካው ውሸት አንግበው መጥተዋል። የኢትዮጵያ ሕዝብ የወያኔን ዘረኛ አገዛዝ እስከ ግሳንግሱ አሽቀንጥሮ ለመጣል በሚያደርገው መራራ ትግል፥ ቀዝቃዛ ውሃ ለመጨመር፥ ይህ ነው የማይባል የፕሮፓጋንዳና የሀሰት ውዥንበር በማሰራጨት ላይ ናቸው። በመሆኑም፥ የሕዝቡን የትግል ስልትና ስትራተጂ እነርሱ ሊወስኑለት ይፈልጋሉ። በሰላም ብቻ መታገል ነው የሚያስፈልገው ሲሉም የሥርዓቱ ነፍስ አዳኝ ሚና ለመጫወት ይሻሉ። የጀግናውን የኢትዮጵያን ሕዝብ ዝናር ለማስፈታት ይደክማሉ። ይህ ግን የሚሆን አይደለም።

ለብሔራዊ ዕርቅ የሚያስፈልጉ መሠረታዊና ዐበይት ነገሮችን ወደ ጎን በመተው እንዲያው ለይስሙላ ብቻ በደፈናው የብሔራዊ ዕርቅ መፈክር አንግበው በየስብሰባው የአዞ ዕንባ ለማልቀስ ይሞክራሉ።
" እነርሱ ጥሬ ስጋ መብላት እንጅ ውጊያማ የት አባታቸው ይችላሉ። እኛ ግን መዋጋት ብቻ ሳይሆን ጦርነት መስራትም አንችላለን" ሲሉ በተመጻደቁበት አፋቸው፥ ዛሬ ስለሰላም ጠቃሚነት ለመስበክ ይጥራሉ። ስየ አብረሃ ዛሬ በሚያደርገው ንግግርና አካሄድ ለመጸጸት እራሱን አላዘጋጀም። በጫካ ሳለ ከወያኔ ጋር ሆኖ ስለ ፈጸመው ብሔራዊ ወንጀልና ክኅደት እንደማዘንና እንደ መጸጸት ፋንታ፥ እርሱም ሆነ ድርጅቱ ወያኔ "የአለፈውን ሂሳብ ለማወራረድ" ፍላጎቱም ሆነ ዝግጅቱ እንደሌላቸው በማያሻማ ቋንቋ ይናገራል። እንዲያውም ይግረማችሁ ብሎ፥ በኢትዮጵያ ውስጥ ለነበረው ጥፋትና አሁንም ስለሚከናወነው የጥፋት ድርጊት በሌሎቹ ላይ ለመለጠፍ ዓይናቸውን በጨው አጥበው ያለ ሀፍረት ለማስረዳት ይሞክራሉ። ኢሕአፓ ነው በትግራይ ጦርነት የከፈተብን ብለው በባዕድ ራዲዮ የለፈፉት አንድ ምሳሌ ነው።
ኅሊና ብቻ ሳይሆን፥ ቆጭትም ለሚሰማው ለማንኛውም ዜጋ፥ ይህ ሁኔታ እጅግ የሚያሳዝንና የሚያስገርም ክስተት ይመስለናል። የኢትዮጵያን ሕዝብ እስከ መቸ ድረስ "ገድሎ እግዚአብሔር ይማርህ" እየተባለ እንደሚቀጥል ይገርመናል።

በበኩላችን፥ ግለሰቦች የነበሩበትን ወንጀለኛ ስብስብ እየጣሉ መውጣታቸውን የምንደግፈው ነው። ከሕዝብ ጎራ መደባለቃቸው ግን በቅድሚያ ፀፀትንና አጥፍተን ነበረ ማለትን መጠየቅ አለበት። ከሁሉም በላይ ደግሞ፥ እውነትም ያንን የወንጀለኞች ጎራ ጠልው ወደ ኢትዮጵያ ሕዝብ ጎራ መጥተዋል ወይ? የሚለው ጥያቄ በሚገባ ተጣርቶ መልስ ማግኘት አለበት። ከወያኔ ተለየን ብለውና ተቃዋሚ መስለው የቁርጡ ቀን ሲመጠማ ደግሞ፥ ከጳጳሱ በላይ ካቶሊክ እንደሚባለው፥ ከወያኔም በላይ ወያኔ ሆነው ሲለፍፉ የሰማናቸው ጥቂቶች አይደሉም። ከዚህ በተያያዘ ደግሞ ያለፈ- ያገደመውን ሁሉ የሕዝብ ጀግና ብለው እላያችን ላይ ሊጭኑ የሚቻኮሉትን አደብ ግዙ ከማለት አልፎ፥ ድርጊታቸው ጥርጣሬን የሚያስነሳ ነውና ሚናቸውንም መመርመር እንገደዳለን። የሕዝብን ጀግና ሿሚዎች ማን እንዳደረጋቸው አይታወቅምና፥ ሕዝብ የራሱን መሪና ጀግና በራሱ ሚዛን መዝኖ፥ ፈትኖ፥ ገምግሞና በይኖ

ሊሰይም መቻሉን በጊዜ እንዲረዱት ያስፈልጋል፡፡ ሕዝብን ዘወትር ለማታለል መነሳት ወንጀል ከመሆኑ ሌላ ፍሬ አይኖረውም፡፡ ከንቱ ድካም ነው፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ ደግሞ የበለፀገ ታሪክ ያለው በመሆኑ፥ በአፍለኛ የፖለቲካ ጮሌነትም ሆነ በተልካሻ ፕሮፓጋንዳ የሚፈታ ሕዝብ አይደለም፡፡
ለነፃነቱ ትግል፥ ማን ደሙን እንዳፈሰሰለት ፥ ማን ደግሞ የአዞ እንባ እንደሚያለቅስ በሚገባ ያውቀዋል፡፡ የበግ ለምድ በመልበስ፥ በተለየ መልክና ቅርፅ ወያኔዎቹ እንደ እባብ ቆዳቸውን እየሸለቀቁ በአዲስ ቆዳ ለመታየት ሲፍጨረጨሩ በአርምሞ አንመለከታቸውም፡፡ የከይሴዎችንም ዳግም ምፅዓት እየተከታተልን እንዋገዋለን፡፡ ለሚቀጥለው የወያኔ ምርጫ የሚያቋምጡትንም የኢትዮጵያን ሕዝብ ትግል እንዳያኮላሹት የዜግነት ምክራችንን አበክረን እናስተላልፍላቸዋለን፡፡ ሰማይ ዝቅ መሬት ከፍ ቢልም የኢትዮጵያ ሕዝብ በመጨረሻ እንደሚያቸንፍ በዕርግጠኝነት መናገር እንችላለን!!!